# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ <u>ከዚኽ ወዴት</u>?

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

<u>***ክፍል ስድስት** (ከክፍል አምስት የቀጠለ)*</u>

<u>**ሐ - ፩፡- የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ኢዴኃቅ)...፤**</u>

በተጨማሪም ከዚኽ በላይ እንዳየነው ኢዴኃቅ እንደ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ስብስብ ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ ላይ የተያያዘውን የጥፋት አቅጣጫ ለማስቀየርና ለአገር አንድነትና ለሕዝባዊ ሥርዓት እውን መሆን የሚያደርገው ትግል ሁል-አቀፍ እንዲሆንና የበለጠ እንዲጎለብት በማሰብ፣ በሱ (በኢዴኃቅ) ውስጥ ያልተካተቱና በአገሪቱ ላይ ለውጥ እንዲመጣ የሚሹ ፀረ-ኢሕአዴግ ኃይሎች እንዲሰባሰቡ ያልተቋረጠ ጥረት አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን እንደ ኢሕአዴግ ጎሣን/ቋንቋን መሠረት ባደረገ ፍልሥፍና የተደራጁ፣ በአንድ አውራ ድርጅት (በሕወሓት) ፍፁም የበላይነትና ሙሉ ቁጥጥር የሚሽከረከሩ አባል ድርጅቶችን ያቀፉ ሣይሆን፤ ከምሥረታቸው ጀምሮ ኅብረ-ብሔረሰብ፣ እምነታቸውና ራዕያቸው አገር-አቀፍና ኢትዮጵያዊ የሆኑ ድርጅቶች የተካተቱባቸው፣ ሙሉ ድርጅታዊ ነፃነት ያላቸው፣ በራሣቸው በጎ-ፈቃድ ብቻ የተሰባሰቡ ኃይሎችን ያቀፉ የጋራ ትግል መድረኮች (ስብስቦች) ቢሆኑም፣ በኢዴኃቅ አነሳሽነትና ግንባር-ቀደም ጥረት የተቋቋሙ የተቃዋሚው ጎራ ስብስቦች መሠረታቸውን የጣሉት ከሞላ-ጎደል የኢሕአዴግን የአደረጃጀት ዘይቤ በተከተለ መልኩ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይኽ ደግሞ ሆን ተብሎና የኢሕአዴግ ነፀብራቅ ለመሆን ታስቦ ሣይሆን በዚያን ጊዜ የአደረጃጀት ዘይቤዎች በወቅቱ የነበረውንና አሁን ድረስ የቀጠለውን የጎሠኝነት ጠገግ የተከተለ ስለነበርና የሚደረጉ መሰባሰቦች ሁሉን-አቀፍ መሆን ስላለባቸው እንደ ኦነግ ቀደም-ሲል የነበሩትንም ይሁን አዲስ የተፈጠሩትን እንደ ትግራይ-ትግርኚ፣ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ትዴት)፣ ወዘተ.. የመሣሰሉትን ማግለል በስልትም ይሁን በመርኅ ደረጃ የሚሆን አልነበረም፡፡

እነኝህ የተቃዋሚው ጎራ ስብስቦች በነበረችው ትንሽ ገርበብ ባለች የመፈናፈኛ የፖለቲካ ምኅዳር በአገር ውስጥ በመደራጀት ከአገዛዙ "ሕጋዊ" ፈቃድ ተሰጧቸው የሚንቀሳቀሱና ያችም ቀዳዳ ጥርቅም ብላ የተዘጋችባቸውና ግልፅ እንቅስቃሴአቸውን በውጭ አገሮች ያደረጉ ድርጅቶችን አሰባጥረው ያቀፉ ስለነበር፤ ሁለቱን ክፍሎች በአንድ አስገዳጅነት ያለው የጠበቀ መዋቅራዊ ትስስር ውስጥ አስገብቶ ሁኔታው የሚጠይቀውን ጠንካራ ትግል ለማካሄድ እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ በጋራ እንቅስቃሴው ላይ አሉታዊ ጫና ማስከተሉ የግድ ነው፡፡ ከዚኽም በላይ እነኝህ ስብስቦች በውስጣቸው ያቀፏቸው አባል ድርጅቶች በትግል ስልትም ይሁን በትግሉ ልዕለ-ግብ ላይ "ያለው አገዛዝ አምባ-ገነን መሆን፣ የአገሪቱ ሁኔታ እንዲቀየር፣ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ እንዲቋቋም፣..." ከሚል ደፈናዊ አቋም-ገላጭና ምኞት-አዘል "መግባባት" ውጭ ለምሳሌ መሠረታዊ የሆነውን የአገዛዙን "ሕገ-መንግሥት" በተመለከተ ኢዴኃቅ ባቀፋቸው ድርጅቶች መኻል የነበረውን ያኽል ተመሣሣይ የሆነ የማያሻማ አቋም አልነበራቸውም፡፡ በነዚኽና በሌሎች ምክንያቶች ያ ዓይነት አደረጃጀት ውሎ አድሮ ችግር ማስከተሉ አልቀረም፤ ስለሆነም ይኽ ጊዜው የፈጠረው አሉታዊ ሁኔታ ኢዴኃቅ ወቅቱ የሚጠይቀውን ወሳኝ ትግል ለማድረግ አላስቻለም፡፡

*3. የትግል ትልም (ስትራቴጂ)፤-* ከኢዴኃቅ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአጠቃላይ በአዎንታዊ ለውጥ ፈላጊው ጎራ በኩል ያለውን የኃይሎች መሰባሰብን በተመለከተ የታየውና የሚታየው አካሄድ የሚያሳየን መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ የተመሠረተ አዲስ

አደረጃጀትና ቅኝት እንዳልተያዘ ነው። ይኸ ምናልባት የአገዛዙን ድርጅታዊ ተፈጥሮም ይሁን የፖለቲካ ፍልሥፍናና ይዞታ በተገቢ ጠንቅቆ ካለመረዳት ወይም የተጋፈጥነውን ዙሪያ-ጥምጥም ችግር ስፋትና ጥልቀት አቅልሎ ከማየት ሊመነጭ ይችላል።

ኢ.ዴ.ኃ.ቅ የተቋቋመው የደርግ መውደቂያ ዋዜማ ላይ የአገራችን ዕጣ-ፈንታ በውጭ ኃይሎችና በተወሰኑ ፀረ-አንድነትንና መገንጠልን ዓላማቸው አድርገው በያዙ ክፍሎች የሚወሰንበት፣ የአገር አንድነትና የሕዝብ ሰላምና መረጋጋት እጅግ አሳሳቢ በሆኑበት እጅግ ፈታኝ ወቅት በመሆኑ፣ ለሁኔታው አስፈላጊውን ምላሽ ለመስጠትና ሕዝብን ከትርምስ፣ አገርን ከመከፋፈልና ከአጠቃላይ ቀውስ ለማዳን ሁሉንም ያቀፈ የሽግግር መንግሥት የሚቋቋምበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ነበር። ይኸ ዓላማ እውን እንዲሆን የታጠቁና ቢጠሩ አቤት የማይሉ በፈረጠመ ጡንቻቸው የተማመኑ፣ ድል ዋዜማ ላይ ያሉና የተለየ ዓላማ ያላቸው ኃይሎችንና በጎ-ፈቃድና ፍላጎት እንጂ አስገዳጅ ኃይል ያልነበራቸው አገር-ወዳድና ሕዝባዊ የአንድነት ኃይሎች፣ እንዲሁም በነዚኽ ሁለት ኃይሎች መኻል የሚገኙ ክፍሎችን ማቀራረብን ይጠይቃል። ይሁንናም በግትርነታቸው፣ በትዕቢታቸውና በዕብሪታቸው ወደር-የለሽ መሆናቸው የተመሰከረላቸው የሕወሓት/ኢሕአዴግና የሸዓብያ መሪዎች ሁኔታዎችን እንዳሻቸው ማሽከርከር የሚያስችላቸውን ሥልጣን ሲይዙ ይኸ የኢ.ዴ.ኃ.ቅ በጎ ራዕይ እነዚኽን ኃይሎች በጨመረ መልኩ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል የታወቀ ነበር። በተጨማሪም ኢ.ዴ.ኃ.ቅ የተከተለው የትግል ስልትና ትልም ከመነሻው ከያዘው ያልወጣና ለነበረው የተለወጠ ሁኔታ መጣኝ እንዲሆን በሚገባ ተጠንቶ ያልተቀናበረ በመሆኑ "እባካችሁ ስሙኝ" ላይ ያተኮረ አቤት-ባይ ከመሆን ማለፍ ባለመቻሉ እነዚኽ አፍላ ጉልበተኛ ኃይሎች ሰከን ብለው ወደ ውይይት ፊታቸውን እንዲያዞሩ በሚያስችል መልኩ እያደገ የሚሄድ የተጠናከረ ሕዝባዊ ኃይል ለማንቀሳቀስ አቅምም ሆነ ይዞታ አልነበረውም።

ይኸ አገር እንዳትፈርስና ሕዝብ ለትርምስ እንዳይዳረግ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም የተቋቋመ ድርጅት፣ አደረጃጀቱም ያንንኑ የሚያንፀርቅ እንዲሆን የግድ ይላል። የተከተለውም የትግል ስልት ይኸንኑ ዓላማ በተግባር ለመተርጎም የሚያስችለውን እንዲሆን ይጠበቃል። ምንም እንኳን እየተለወጠ ለሄደው ሁኔታ ብቁ ሆኖ ለመገኘት ኢ.ዴ.ኃ.ቅ ውስጣዊ አደረጃጀቱን ለመቀየር ጥረት ቢያደርግም፣ የሚከተለው የትግል ትልምና ስልት ላይ ብዙ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችለውን አደረጃጀትና አወቃቀር ማግኘት አልቻለም።* ኢ.ዴ.ኃ.ቅ የተከተለው የትግል ትልም በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ያሉ ድርጅቶችን አስተባብሮ "ፀረ-ኢሕአዴግ" ጎራውን በማጠናከር አገራዊ እርቅና ሰላም ሂደትን በመከተል በአዲስ የሽግግር ሂደት ፈር የለቀቀውን የዴሞክራሲ ሂደት በማስተካከል ላይ የሚሽከረከር ነበር። ስልቱም ሰላማዊ ነበር። በዚኽ ጥረቱ ረገድ በብዙ አንገብጋቢ፣ አሳሳቢና አደገኛ ርዕሰ-ጉዳዮችና ወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎችን እያወጣ ማሰራጨት በመቻሉ በጊዜው የነበሩ ብቻ ሣይሆን ወደ-ኋላ የተፈጠሩ ድርጅቶች ለሚያደርጉት ሰላማዊ ትግል ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳደረገ አሌ አይባልም።
ሆኖም ሁኔታዎች እየተቀየሩ፣ አገዛዙም ተቃዋሚው በሚያደርገው ጥረት ከእቅዱ ሳይፈናቀል ጎን ለጎን ሆኖም ወደ-ላይና ወደ-ታች የያዙትን ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ኢ.ዴ.ኃ.ቅም

*(*1ለጉዳዩ መፍትኄ ለማስገኘት ብዙ የውስጥ ምክክሮች ተደርገዋል፣ አንዳንድ እርምጃዎችም ለመውሰድ ተመክሯል። አንደኛው ሙከራ ከኢሕአፓና ከመኢሶን ውጭ ያሉ ድርጅቶች በአብዛኛው ከመኻል ወደ-ቀኝ ያዘነበለ አመለካከት ያሏቸው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ክፍሎች ስለነበሩ እነሱን በአንድ ድርጅት ሥር ለማጠቃለልላ ቆይቶም በሲቪክና በሙያ ስብስብ ስም ካሉት ውስጥ እርባና ያላቸውንና ከአገር-ወዳድ ግለሰቦችን በጨመረ መልኩ በማደራጀት በኢ.ዴ.ኃ.ቅ የተጀመረውን የግራ ትግል በአዲስ መንፈስና ቅኝት ለማጠናከር ታስቦ ብዙ ወራት የፈጀ ውይይት ተደርጓል። ግቡም ዞሮ ዞሮ በሁለት የአስተሳሰብ አዝምሚያዎች የተደራጁ (መኻል-ቀኝና መኻል-ግራ) ሆነው ጠንካራ ማዕከል ያለው ድርጅት እንዲሆን ነበር። ሆኖም የተወሰነው ክፍል በኋላ የጋራ ትግሉን ለማጠናከር ከታሰበው ውጭ "መድኅን" በሚል ስያሜ ሲለይ፣ የቀረው ክፍል በኢ.ዴ.ኃ.ቅ ውስጥ ከነበሩት ድርጅቶች ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራቲክ አንድነት (ኢ.ሕ.ዴ.አ) እና የኢትዮጵያ ፌዴራል ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኢ.ፌ.ዴ.ፓ) በተለያየ ደረጃና መስክ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ትግል ተካፋይ የነበሩ ታዋቂ አገር-ወዳዶችን በማከል ተዋኅደው "የኢትዮጵያ ሕዝብ ፌዴራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፓርቲ - ኅብረሕዝብ-ኢትዮጵያ" በኢ.ዴ.ኃ.ቅ የሚደረገውን የጋራ ትግል ለማጠናከር ተሞክሯል)።*

የተደቀኑበትንና ተብትበው የያዙትን መሠረታዊ የአደረጃጀትና የአወቃቀር ይዞታ ሳይፈታና ሣይቀይር እንደ ኢዴኃቅ የወቅቱ ሁኔታ በሚጠይቅ መጠን አስተማማኝ ውጤት ሊያመጣ በሚችል መልክ የትግል ትልሙንም ሆነ ስልቱን ለመቀየር አልቻለም፤ አይችልምም ነበር።

እንግዲኽ የትግል ትልምና ስልት ለመቀየር ውስጣዊ የአደረጃጀትና የአወቃቀር ለውጥ ማምጣት አስፈላጊነት እንደጠንጠለጠለ ነው ኢ.ዴ.ኃ.ቅ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመሆን ለውጥ ለማምጣት ጥረቱን የቀጠለው። ይኽ ሁኔታ በተገቢ ባለመጤኑ ሊሆን ይችላል የበርካታ ድርጅቶች ስብስብ የሆነው ኢ.ዴ.ኃ.ቅ በኢ.ዴ.ኃ.ቅነቱ - እንደ አንድ ስብስብ - ከሌሎች ኃይሎች ጋር በሚደርገው መሰባሰብ በአገሪቱ ላይ ለውጥ ለማምጣት ከሚጠይቀው የአደረጃጀትና የትግል ስልት ጥያቄ አኳያ እራሱ እንዲፈጠሩ ባሰባቸውና በደከመባቸው የኃይል ስብስቦች ውስጥ የሚኖረው ሚና፣ በውስጡ ባቀፋቸው ድርጅቶችና አዲስ በሚሰባሰቡት ኃይሎች መኻል መኖር ስላለበትና ስለሚኖርበት የአሠራርና የትስስር ሁኔታ በጥልቀት ያልታሰበበት አካሄድን መከተሉ አልቀረም።

ሁኔታው የኃይሎች መሰባሰብን የግድ የሚጠይቅ እንደመሆኑ፣ ኢ.ዴ.ኃ.ቅ ከሱ ውጭ ካሉ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ወሳኝ ትግል ለማድረግ ሲያስብ አንድም በተቻለ መጠን ሁሉንም ያካተተ የጋራ የትግል መድረክ እንዲሆን ታልሞ በተመሠረተበት መንፈስ ሌሎቹ በሱ ውስጥ እንዲካተቱ ማሳመን አለያም በኋላ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢ.ዴ.ኃ.ኅ) ሲመሠረት እንደተደረገው እራሱን በትኖ አዲስ የኃይሎች ስብስብ በአዲስ መልክ እንዲደራጅና እንዲዋቀር መጣር ሲኖርበት፣ የሚፈጠሩ ስብስቦች የድርጅቶችን ቻም-ለቻምም ባይሆን እኩል ተሣትፎ የሚጠይቅ ስብስብ ሆኖ እያለ በተደራጀ ስብስብ ላይ ሌላ ስብስብ እየተጨመረ የስብስብ ድባሎ በመሆኑ በአወቃቀርም ይሁን በአሰላለፍ ችግር ማስከተሉ አልቀረም። ስለሆነም ኢ.ዴ.ኃ.ቅ እራሱ የድርጅቶች ስብስብነቱን እንደጠበቀ ነበር መጀመሪያ ፓሪስ አንድና ከዚያም ፓሪስ ሁለት በተደረጉትም ይሁን የኢትዮጵያ አገራዊ ጉባዔ በሞከረው የጋራ መድረክ ውጥኖች የተሣተፈውና አዳዲስ የመሰባሰብ ሙከራዎችን ለመቀጠል የወሰነው። ይኽ አካሄድ የስብስቦች ድርብርቦሽን በመፍጠሩ በተለይ በኢተፖድጎና በአማራጭ ኃይሎች የጋራ ጥረቶች ላይ መዘበራረቅን መፍጠሩና ችግሮችን ማስከተሉ የማይቀር ጉዳይ ነበር። ለምሣሌ "ኢ.ሕ.ዴ.ግንና ተቃዋሚውን ክፍል ለማቀራረብ፣ ለማነጋገርና ለማደራደር" በሚል በአሜሪካ ምክር ቤት የአፍሪቃ ጉዳይ ንዑስ ኮሚቴ አማካይነትም ሆነ በዋይት ሐውስ እንዲሁም በካርተር ማዕከል በተድረጉ ስብሰባዎች ላይ የድርጅቶች ስብስብ የሆነው ኢ.ዴ.ኃ.ቅ እራሱ እንዲፈጠር የደከመበትና ከሞላ-ጎደል ሁሉንም በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፉ ድርጅቶችን በአባልነት አቅፎ በያዘው የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ተወክሎ እንዲገኝ ማድረጉ አስፈላጊ፣ ተገቢና የጋራ ትግሉን የበለጠ የሚያጠናክር እርምጃ በመሆኑ ያም ተግባራዊ እንዲሆን በተለይ የሁሉም ድርጅቶች በተወከሉበት የሰሜን አሜሪካው የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አማካይነት የተደረገው ከፍተኛ ጥረት በኋላ እንደምናየው በአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ኃላፊዎች ዘንድና በኢ.ዴ.ኃ.ቅም ውስጥ አንዳንድ ድርጅቶች ሳይቀበሉት ስለቀረ ተግባራዊ ሣይሆን ቀርቷል። ያ አጋጣሚ ጥቅም ላይ ሣይውል እንዲሁ በመባከኑም ድርጅቶች ደክመው የሚመሠርቷቸው የጋራ ትግል መድረኮች እርባናና ጥቅም እምኑ ላይ እንደሆነ ትርጉም እያጣና በአባል ድርጅቶች መኻልም ሙሉ መተማመን እንደሌለ የሚያሣይ በመሆኑ በጋራው ትግል ላይ አሉታዊ ጫና ማሳደሩ የግድ ነበር።

ሁነኛና አስተማማኝ ለውጥ የሚያስገኝ ትግል ለማድረግ ቅድሚያን ከእጅ ያልለቀቀና በመስክ ላይ ያለውን ሁኔታ መቀየርን የግድ ይላል። ይሁንናም ኢ.ዴ.ኃ.ቅ የተከተለው ስልትም ሆነ አጠቃላይ በአገሪቱ የሰፈነው ሁኔታ ቅድሚያ ከእጁ እንዳይወጣና አገዛዙን ተከላካይ ማድረግ የሚያስችል አልነበረም። ቀደም-ሲል እንዳየነው ለጊዜው ከነበረው በአብዛኛው ለለውጥ ኃይሎች ትግል አሉታዊነቱ ያመዘነ አጠቃላይ የአካባቢም ሆነ ዓለም-አቀፍ ሁኔታ በተጨማሪ፣ የኢ.ዴ.ኃ.ቅ አወቃቀር አንድ ወጥ አደረጃጀትንና አመራርን

የሚጠይቅ የተጠናከረ የትጥቅ ትግል ለማድረግ ችግር ነበር፡፡ ሕዝብን በስፋት አደራጅቶ አገዛዙ በሕዝባዊ ነውጥ ተገድዶ እርባና ወዳለው ድርድር እንዲመጣ አለያም ጭራሹን እንዲንበረከክ ለማድረግ የሚያስችል እግር-ተከል ትግል ለማድረግም ከአባል ድርጅቶች በጎ-ፈቃድና ቁርጠኝነት ውጭ እንደ ትጥቅ ትግሉም ባይሆን ኢዴኃቅ የያዘው የትግል ትልምና ለዚሁም የያዘው አወቃቀር ምቹ አልነበረም፡፡

ሆኖም ኢዴኃቅ የተመሠረተበት ዓላማ አልፎት እንደሄደና በያዘው አደረጃጀት፣ አወቃቀርና አሠላለፍ ያሰበውንና የሚታገልለትን ለውጥ ለማስገኘት እንደማይችል በተገቢና በጊዜው ሣያጤነው፣ የአባልቱን ከፍተኛ የአገር-ወዳድነት መንፈስ፣ ቁርጠኝነትና ዝግጁነት እንደያዘ የሕዝብን ቀልብ የሚስብና አመኔታ የሚያድስ እየፋመና እየጋመ የሚሄድ ሕይዎት ያለው እንቅስቃሴ ለማድረግ ሳይችል፣ ድንጋዩ እንዳለቀበት ባትሪ ወይም እንደ ደነበሸ ጥይት ቀፎውን ይዞ መንገታገት ዕጣው ሆነ፡፡ በመሆኑም የአገር አንድነት እንዲከበርና የዜጎች መብት እንዲጠበቅ ያለውን በጎ-ፈቃድና የማይናወጥ እምነት ሳይለቅ ለተቀየረ ሁኔታ ያልተለወጠ አደረጃጀትና የትግል ስልት ይዞ ለመቀጠል ማሰቡ በራሱ ላይ የሰመመ ክስመትን ማስከተሉ አስከትሏል፡፡ ቅንጅቱ ከወደቀበት ከዚያ አጣብቂኝና የተሟዘዘ ጉዞ ለማላቀቅና ትግሉን በተነድሶ ለማስቀጠል በማሰብ ከኢዴኃቅ አባል ድርጅቶች የተወሰኑት ከኢዴኃቅ ውጭ ካሉ እንደ "የቤኒ ሻንጉል የነፃነት ግንባር" ከመሰሉ ጋር በመሆን "ኢአግ" በሚል የትጥቅ ትግል ለማድረግ ሞክረዋል፡፡ ሆኖም ያ አካሄድ በኢዴኃቅ አባል ድርጅቶች መኻል ይበልጥ ልዩነትን አስከትሏል፡፡

*4. የአመራር ችግር፡-* የአገራችንን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት በአሁኑ ጊዜ በሥልጣን ላይ የሚገኘውን የአገዛዝ ተፈጥሮ ባኅሪ ግምት ውስጥ ያስገባ ወሳኝ ሕዝባዊ ትግልን እንደሚጠይቅና ያም ሕዝባዊ ትግል በአንድ መሠረተ-ሠፊና ጠንካራ አገር-አቀፍ ድርጅት ማዕከልነትና መሪነት መደረጉ በጣም አስፈላጊ መሆኑ በሕዝባችን ዘንድም ሆነ በአገር-ወዳድና ዴሞክራት ወገኖች ዘንድ ብዙ ላያከራክር ይችላል፡፡ አደረጃጀቱና አወቃቀሩ ከሚከተለው የትግል ትልምና ስልት ጋር በአገሪቱ ለሰፈነው ሁኔታ ምላሽ ሰጭ እንዲሆን ደግሞ ተጠያቂነት ያለው፣ የበሰለ፣ የማያኅበድድና በእምነቱ የጠና ጠንካራ አመራርን ይጠይቃል፡፡ የአንድ ድርጅት አደረጃጀትና አወቃቀር የአመራሩን ሁኔታ በማመቻቸትና ይሁን ለፍሬ በማብቃትም ይሁን አምባ-ገነንና መና በማድረጉ ረገድ ከፍተኛ ቦታ አለው፡፡ በግልባጩም ድርጅትን እንዲመራ የኃላፊነት የተሰጠው ሰው ወይም ክፍል የተበላሸውን አሻሽሎ፣ የተለያየውን አገናኝቶ፣ የተሰበረውን መንፈስ ጠግኖ፣ የትግል ወኔን ቀስቅሶና አነሳስቶ ድርጅቱን ለታሰበው ውጤት በማብቃቱም ሆነ በአጉል ትዕቢት ተወጥሮ፣ የድርጅቱን ሣይሆን የግሉን ዝና ፈላጊ ሆኖ፣ የሕዝብን ጥቅም ሣይሆን የራሱን ጠባብ ፍላጎት በማራገብ የአባላቱን ድካምና የሕዝብን ተስፋ መና በማስቀረት ድርጅቱን ሊያንኮታኩት ይችላል፡፡

በኢዴኃቅ በኩል የነበረው አደረጃጀትና መዋቅር ድርጅቱን እንዲመሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ወገኖች የሁሉንም አባል ድርጅቶች ሙሉ አመኔታ እንዲያተርፉ ያላስቻለና የሚጠበቀውን ውጤት ለማስገኘት የሚችሉበትን ሁኔታ ያላገኙ ነበሩ፡፡ ቅንጅቱ ከምሥረታው ጀምሮ እስከ ከሰመበት ጊዜ ድረስ ሁለት ሰዎች በሊቀ-መንበርነት መርተውታል (አቶ መርሻ ዮሴፍና ድ/ር ሙሉጌታ ሥዩም)፡፡ እነኝኽ ሁለት ሰዎች እንደ ማንኛውም ሰው የየግላቸው ደካማና ጠንካራ ጎን ሊኖራቸው ቢችልም፤ የኢዴኃቅ ችግር ግን ከግለሰቦች የዘለለ መሠረታዊ የአደረጃጀትና የአወቃቀር ስለ-ነበር በነሱም ላይ ሆነ በአመራር አካሎች (ኮሚቴዎች) ላይ ብዙ መተቸቱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

***በክፍል ሰባት ይቀጥላል……***